# <u>አስናቀ እንግዳ ይድረስህ ምስጋና</u>

አስናቀ እንግዳ
ገና ከጠዋቱ፡ ጎህ እንደቀደደ፡ ገና በማለዳ
ከቆላ ከደጋ ተሸክሞ ዕዳ
ከደቡብ ከሰሜን
ከምዕራብ ከምሥራቅ ዘልቆ በመደዳ
ለሀገሩ ለቀዬው ሰው እንዳይሆን ባዳ
አበው ያወረሱት ታሪክ እንዳይጠፋ
መላውን ዕድሜውን ያለ ቀና ደፋ
ሀሰትን ኮንኖ፡ ሀቅን ይሚያፋፋ
ምዝበራን ተጋፍጦ፡ ለሕዝብ የተዋጋ
አልገዛም ያለ ላምባገነን መንጋ
ሕይወቱን አስተምሮ፡ ሕይወትን እየኖረ
ንዋይ፡ ሀብት፡ ዝና ከቶ ያላፈቀረ
የዕድሜ ባለጸጋው ጀግናው የእንግዳ ልጅ
ይድረስህ ምስጋና ከዚህ ካሲምባ ድጅ
ከዘመድ ከወዳጅ።

ያገር ፍቅር ስሜት ውስጡን እየበላው
የወገኑ ብሶት እያብከነከነው
የሰንደቁ ክብር እያንገበገበው
ኢትዮጵያ ታሪኳ ተከብሮ እንዲኖር
አንድነቷ ጸንቶ እንዲሆነን ማገር
ሉዓላዊነቷ ጸንቶ እስከዘላለም
የሕዝቧ አንድነት እንዲኖር እስካለም
ታግሎ ያታገለ፡ መካሪ የረቀቀ
ከቶ ወዴት አለ እንዳተ አስናቀ።

የግፍ አገዛዝን፡ ጭቆና ምዝበራ
መከራና እምባ ከቶ እንዲባራ
ከአድሞአችን እንዲጠፋ በሽታና ረሃብ
ዕድሜህን የኖርከው ቆመህ ለሀገር ዘብ
እኮ የት ይገኛል ይህን ሁሉ ዘመን
ከቶ ሳይሰለች ለሕዝብ ሲብከነከን።
አሟጦ የሰጠ ሕይወቱን ለሀገር
ለፊውዳል ጥሪ ፊቱንም ሳያዞር
በፋሽስቶች ሴራ ላፍታ ሳይሸበር
በጎጠኞች ወጥመድ ከቶ ሳይበገር
በሀገር ጠላቶች ቅስሙ ሳይሰበር
በጽናት የቃኘ የሀገርን ዳር ድንበር
ከቶ የት ይገኛል የሀገር ወታደር።
አስናቀ እንግዳ
ገና ከጠዋቱ፡ ጎህ እንደቀደደ፡ ገና በማለዳ
ከቆላ ከደጋ ተሸክሞ ዕዳ
ከደቡብ ከሰሜን
ከምዕራብ ከምሥራቅ ዘልቆ በመደዳ
ለሀገሩ ለቀዬው ሰው እንዳይሆን ባዳ
አበው ያወረሱት ታሪክ እንዳይጠፋ
መላውን ዕድሜውን ያለ ቀና ደፋ
ሀሰትን ኮንኖ፡ ሀቅን ይሚያፋፋ

ምዝበራን ተጋፍጦ፡ ለሕዝብ የተዋጋ
አልገዛም ያለ ላምባገነን መንጋ
ሕይወቱን አስተምሮ፡ ሕይወትን እየኖረ
ንዋይ፡ ሀብት፡ ዝና ከቶ ያላፈቀረ
የዕድሜ ባለጸጋው ጀግናው የእንግዳ ልጅ
ይድረስህ ምስጋና ከዚህ ካሲምባ ድጅ
ከዘመድ ከወዳጅ።

ጸንተህ የታገልህ ሦስት የመከራ ዘመን
ጨለማ ተገፎ፡ እንዲስፍን ብርሃን
ተዋጊ ባርነት፡ ነፃነት አፍቃሪ
ሀገርህን ወዳድ፡ ጠላት አሳፋሪ
ጠላት አባራሪ
ለፊውዳል ቅኝት፡ ለቡርዣ ከበሮ
ለስምና ዝና፡ ለተጫፍሮ ኑሮ
ለክብር ለንዋይ፡ ሳትሰጥ ቀጠሮ
እንዳሰማህ ያለህ የሕዝብን ሮሮ
እንደማሰንክ ኖረህ ጋራ ሸንተረሩን፡
ቋጥኙን እሾሁን፡
ዳጋውን ቆላውን፡
ይዘህ ተሸክመህ ብሶት መከራውን
አታግለህ የታገልክ፡ ቆፍጣናው ኮለኔል
እኔስ ኩራሁ ባንተ፡ እስቲ ዕልል ልበል።

ብርታትህን ሳየው፡ ተስፋዬ ጠነከረ
መላውን ዕድሜህን ወኔህ ያልሰበረ
እምቢኝ ለጎጠኛ ብሎ ዛሬም አለ
እጅ አልሰጥ ለጠላት፡ ከቶም ለቀለለ
ነፃነቴን ብሎ አለ እንደታገለ።
እስቲ ላመስግንህ እንግዳው አስናቀ
ፍቅር የሀገርህ ሚስጥሩ የረቀቀ።

ከበታኝ ወያኔ ከቶም ላላስካካ
በባዕዳን ሸምገላ ፍጹም ሳልመካ
ክብሬን የጠበኩኝ ከመሰሪ ደባ
ለውሸት ላላድር፡ ላለብስ ሀሰት ካባ
ጥጋብ ተሞሽሮ፡ ረሃብ ስፍራ አጥቶ
ብልጽግና አብቦ፡ ድህነት ተንኮታኩቶ
ጤናና ደስታ በበሽታ ስቀው
ይደንቁር አባቱ ድንቁርና ጠፍቶ
ጎሰኝነት ሞቶ፡ አንድነት አብቦ
ባርነት ተገፎ፡ ነፃነት ተውቦ
ክብሯን አስጠብቄ ሀገሬን እምዬ
ምድሪቷንም ስሜ ዘልቄ ከቀዬ
ሰንደቋንም ይዤ ከማማ ላይ ቆሜ
ማየትን እሻለሁኝ በቀሪዋ ዕድሜ
ብለህ ያወጋኸኝ አስናቀ አባቴ
አክሊሌም ይኸው ነው፡ መስቀሌ ጽናቴ
ብለህ ያስተማርከኝ፡ ይኸው ነው ሕይወቴ
ዛሬ ልተርከው አውጥቼ ካንጀቴ።

**አስናቀ እንግዳ ይድረስህ ምስጋና..............አሉላ ከአሲምባ ፓልቶክ...ነሐሴ 10፣ 1999 ዓ.**

አስናቀ እንግዳ
ገና ከጠዋቱ፡ ጎህ እንደቀደደ፡ ገና በማለዳ
ከቆላ ከደጋ ተሸክሞ ዕዳ
ከደቡብ ከሰሜን
ከምዕራብ ከምሥራቅ ዘልቆ በመደዳ
ለሀገሩ ለቀዬው ሰው እንዳይሆን ባዳ
አበው ያወረሱት ታሪክ እንዳይጠፋ
መላውን ዕድሜውን ያለ ቀና ደፋ
ሀሰትን ኮንኖ፡ ሀቅን ይሚያፋፋ
ምዝበራን ተጋፍጦ፡ ለሕዝብ የተዋጋ
አልገዛም ያለ ላምባገነን መንጋ
ሕይወቱን አስተምሮ፡ ሕይወትን እየኖረ
ንዋይ፡ ሀብት፡ ዝና ከቶ ያላፈቀረ
የዕድሜ ባለጸጋው ጀግናው የእንግዳ ልጅ
ይድረስህ ምስጋና ከዚህ ካሲምባ ድጅ
ከዘመድ ከወዳጅ።

ፈደል መቁጠር ብቻ እኮ ዋጋ ካለው
ጮርቃ ያልበሰለ ዕውቀትም ቢኖረው
ዐዋቂ ነው ተባይ፡ ብርቱ ሚመራመር
ሀገሩን የማያውቅ፡ ሲጠሩት ግን በክብር
ስንቱን ያስነበበ፡ ስንቱን ተፈላሰፎ
ሀገር ሲሉት ባዶ፡ ሕዝብ ሲሉት ቀፎ
ይምጣና ይመርምር፡ እዚህ ግኝት አለ
ሳይንስ የማያውቀው፡ ጽናት የተባለ
ዕድሜውን ከሚፈጅ ወሬ እያነጠረ፡ ወሬ እያጠለለ።

ይምጣ ይስተናገድ ካስናቀ ኮሌጅ
ተምሮ ደንቁሮ፡ ለሀገር ማይበጅ
ሀገሩን ይወቃት አይሁንባት ባዳ
አይናቀው፡ አያጥላላው ሕዝቡንም ይረዳ
ያጥብቀው፡ ከፍ ያርገው ያገሩን ባንዲራ
ተምሮ ካስናቀ፡ ከዚህ ከዳብተራ
ከሀገር አባ ወራ።

ሦስት መንግሥት ካዩ፡ ከዓፄው ጀምሮ
እየተገላበጠ ደልቆ ከበሮ፡ ከሁሉም ጋር አድሮ
ከዓፄው ጋር ሆኖ በረሃብ የሳቀ
በበሽታ፡ ድህነት ከቶ የተሳለቀ
ከደርግም አገዛዝ ሄዶ የተጣበቀ
እናት ሀገር ብሎ በሀገር የቀለደ
መኖር ነው እያለ ዳር ዳሩን የሄደ
ወያኔም ሲመጣ እጁን የሰደደ
በሦስቱም አገዛዝ ሆዱን የወደደ
በሀገር አሹፎ በሕዝብ ያላገጠ
እኔስ አፈርኩበት ተማርኩ ያለ ደንቆሮ
ኑሮው የቀበሮ
አደባባይ ውጥቶ ከሚሆን ቀዳዳ

መሄጃው ጠፍቶበት ከሚሄድ ገዳዳ
ይልቁንስ ይማር ካስናቀ እንግዳ
መንገድ ያሳየዋል የሀገሩን ጓዳ።
ሦስት መንግሥት ታግሎ ታሪኩ ሚጻፈው
አንደበተ ርቱዕ ቆራጥ ለዓላማው
ዘላለም ዓለሙን ከሕዝብ ጋር ያለው
አስናቀ እንግዳ ብዙ ትምህርት አለው።

አስናቀ እንግዳ
ገና ከጠዋቱ፡ ጎህ እንደቀደደ፡ ገና በማለዳ
                ከቆላ ከደጋ ተሸክሞ ዕዳ
ከደቡብ ከሰሜን
        ከምዕራብ ከምሥራቅ ዘልቆ በመደዳ
        ለሀገሩ ለቀዬው ሰው እንዳይሆን ባዳ
አበው ያወረሱት ታሪክ እንዳይጠፋ
መላውን ዕድሜውን ያለ ቀና ደፋ
ሀሰትን ኮንኖ፡ ሀቅን ይሚያፋፋ
ምዝበራን ተጋፍጦ፡ ለሕዝብ የተዋጋ
አልገዛም ያለ ላምባገነን መንጋ
ሕይወቱን አስተምሮ፡ ሕይወትን እየኖረ
ንዋይ፡ ሀብት፡ ዝና ከቶ ያላፈቀረ
የዕድሜ ባለጸጋው ጀግናው የእንግዳ ልጅ
ይድረስህ ምስጋና ከዚህ ካሲምባ ድጅ
                        ከዘመድ ከወዳጅ።

አንጋፋ በዕድሜ ባገኘህም ሆነህ
ኮነሌሉ ቀርቶ፡ እምዬ ልበልህ
ማዕረጉን ልተወው፡ አብዬ እንድልህ
መከታ ጋሻዬ፡ እንበልህ ያገሬ
በተግባር ተፈትነህ፡ የቀምከው ከበሬ
ቃላቶች የሉኝም እኔ ላንተ ክብሬ።
አውርሰኝ ቃል ኪዳን ልገዛ በቃልህ
ባርከህ ስጠኝ አርማ፡ እስቲ በለኝ አይዞህ
በርከክ ብዬ ልውሰድ ልጎንበስ ከግርህ
                        ልደፋ ከግርህ።